# ረቂቅ የቁም እንስሳት ግብይት ፖሊሲ



**ንግድና ቀጣናዎች ትስስር ሚኒስቴር**

**-------/ 2015 ዓ፣ም**

**አዲስ አበባ**

**ማውጫ**


***ማውጫ*** ........................................ ***1***

***1. መግቢያ*** ........................................ ***2***

***2. የፖሊሲው አስፈላጊነት*** ........................................ ***3***

***3. የፖሊሲው ዓላማና ግቦች*** ........................................ ***3***

3.1 ርዕይ ........................................ 3

3.2 ግብ ........................................ 3

3.3 ዓላማዎች ........................................ 3

3.4 መርሆዎች ........................................ 4

***4. የፖሊሲ ጉዳዮች*** ........................................ ***4***

4.1 የቁም እንስሳት ግብይት ስርዓት ........................................ 4

4.2 የገበያ ትስስርን በማጠናከር አቅርቦትን ማሳደግ ........................................ 5

4.3 የማበረታቻ ስርዓት ........................................ 5

4.4 የመሰረት ልማት እና ሎጀስቲክስ አቅርቦት ........................................ 6

4.5 ተቋማዊ ቅንጅትና ትብብር ........................................ 7

***5. የፖሊሲው የውጤት መስክ*** ........................................ ***7***

***6. የፖሊሲው ወሰን*** ........................................ ***7***

***7. ፖሊሲ የማውጣት ስልጣን*** ........................................ ***7***

***8. የፖሊሲው የትግበራ ማዕቀፍ*** ........................................ ***8***

8.1 ፈጻሚ ተቋማት ........................................ 8

8.2. የህግ ማዕቀፍ ........................................ 8

8.4. ክትትልና ግምገማ ........................................ 10

***9. ሌሎች ተያያዥ ፖሊሲዎች*** ........................................ ***10***

***10. የፖሊሲው ስርጭት*** ........................................ ***11***

***11. ፖሊሲው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ*** ........................................ ***11***

***12. የቃላት ፍች*** ........................................ ***11***

## 1. መግቢያ

ኢትዮጵያ ካላት የቁም እንሳስት ሃብት ብዛትና ስብጥር በዓለም አቀፉም ሆነ በቀጠናው ከሚጠቀሱት ሀገራት መካከል በቀዳሚነት ትገኛለች፡፡ ምንም እንኳን ሀገራችን በቁም እንሳሳት ሀብቷ በአፍሪካም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ቀዳሚ ብትሆንም ሀብቱን በአግባቡ መጠቀም የሚያስችል አሠራር ባለመዘርጋቱ ይህ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ድርሻ ያለው ሀብት እየባከነ እና በሕገ-ወጥ መንገድ እየወጣ ለጎረቤት ሀገራት ሲሳይ ሆኖ ይገኛል፡፡

የቁም እንሰሳት ሃብት ለኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ ሚና ያለው ሲሆን ለውጪ ምንዛሪ ግኝት፣ ለኢንቨስትመንት፣ ለኢንዱስትሪ ጥሬ እቃ ግብዓት እና ለስራ ዕድል ፈጠራ፣ ወዘተ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ የሆነ እና በሀገራዊ ምርት እድገት ጉልህ ድርሻ ያለው ነው። የቁም እንሰሳትን ንግድ ለመምራት የቁም እንሰሳት የግብይት አዋጅ ተቀርፆ ሥራ ላይ እንዲውል የተደረገ ቢሆንም አዋጁን እስከታችኛው እርከን አውርዶና ግንዛቤ ፈጥሮ ተግባራዊ በማድረግ ሂደት የራሱ የሆነ ውስንነት ስለነበረበት ከዘርፉ እየተገኘ ያለው ገቢ ለሀገራዊ ኢኮኖሚ እድገቱ ያለው ድርሻ ዝቅተኛ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

የቁም እንሰሳት የአቅርቦትና ትስስር ስርዓት አለመዘርጋት፤የግብይት መሰረት ልማት እና ሎጀስቲክስ አለመሟላት፣ የማበረታቻ ሥርዓት አለመዘርጋት፣የቁም እንሰሳት የንግድ ዱካን የተከተለ አሠራር ስርዓት ተግባራዊ አለመደረጉ፣ዘመናዊ የእርባታ ዘዴና የግብይት ሥርዓት ባለመስፋፋቱ፣በዘርፉ የተሰማሩ የንግድ ተዋንያን የስነ ምግባር ጉድለት፣ ወዘተ ምክንያት ዘርፉ ለሕገ-ወጥና ኮንትሮባንድ ንግድ ተጋልጧል፡፡ በዚህም ሀገሪቱ ከቁም እንሰሳት ንግድ ተጠቃሚ እንዳትሆን ተግዳሮት ሆኖ ከመቆየቱም ባሻገር በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚኖረን የገበያ ድርሻና ተወዳዳሪነት ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳርፏል፡፡

በመሆኑም ከቁም እንሰሳት ንግድ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ሀብት በከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግ ግልጽ፣ ተወዳዳሪና ዘመናዊ የቁም እንሰሳት የንግድ ስርዓት የመዘርጋት፣ የሀገር ውስጥ እና የውጪ የቁም እንሰሳት ንግድን ለማሳለጥ የሚያስችል አሠራር ስርዓት የማስፈን፣ የቁም እንሰሳት ንግድ የማበረታቻ ሥርዓት እንዲኖር የማድረግ፣ የቁም እንሰሳትን የወጪ ንግድ መዳረሻ ገበያ የማስፋትና ትስስርን የማጠናከር፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው የቁም እንሰሳት የግብይት መሰረተ ልማት እና ሎጀስቲክስ የማሟላት፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚኖረውን ቅንጅታዊ አሠራር በማጠናከር ሀገሪቱ ከዘርፉ ሊኖራት የሚገባውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እና የገዥ ሀገራትን መስፈርትና ፍላጎት በማሟላት በዓለም አቀፍ የንግድ እድል ተጠቃሚነትን ለማሳደግ እንዲቻል የቁም እንሰሳት ንግድን በአስራር አስደግፎ መምራት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህ የቁም እንሰሳት የንግድ ፖሊሲ ተዘጋጅቷል፡፡

## 2. የፖሊሲው አስፈላጊነት

የፖሊሲው አስፈላጊነት የቁም እንስሳት ንግድ ስርዓትን በማዘመንና ፍትሀዊ ተወዳዳሪነትን በማረጋገጥ ለሀገራዊ ኢኮኖሚ እድገት ያለውን ድርሻ ለማሳደግ ነው ፡፡ይሁን እንጂ በተለያዩ ተግዳሮቶች ምክንያት ሀገራችን ከቁም እንስሳት ሀብት ማግኘት የሚገባትን የውጭ ምንዛሪ ገቢ እና ኢንቨስትመንትን በሚፈለገው ደረጃ ማሳካት አልተቻለም። ዘርፉን በውጤታማነትና በተወዳዳሪነት ለመምራት የሚያስችል ግልጽና ዘመናዊ የአሠራር ስርዓት አለመዘርጋቱና በፖሊሲ አስደግፎ አለመመራቱ ዋነኛ ተግዳሮት መሆኑ ተገምግሟል፡፡

በመሆኑም በቁም እንስሳት ንግድ የሚታየውን የአሠራር ክፍተት በመቅረፍ የሀገር ውስጥ እና የወጪ ንግድ አሠራሩን ግልጽ፣ ፍትሃዊ እና በውድድር ላይ የተመሰረተ፤የግል ዘርፉን ተሳትፎና ድርሻ የሚያሳድግ፤የፋይናንስ አቅርቦትና የማበረታቻ ስርዓትን የተከተለ፤ጥራትን መሰረት ያደረገ ተመራጭና ተወዳዳሪ የቁም እንስሳት የግብይት መሰረት ልማትና አስፈላጊውን ሎጀስቲክስ በማስፋፋት፤የዘርፉን መልካም አጋጣሚዎችና አቅም በስፋት ለመጠቀም ይህን የፖሊሲ ሰነድ ማዘጋጀት አስፈልጓል፡፡

## 3. የፖሊሲው ዓላማና ግቦች

### 3.1 ርዕይ

በ2025 ዓ.ም በአፍሪካ ቀዳሚና ተመራጭ የቁም እንስሳት ንግድ ማዕከል መሆን፡፡

### 3.2 ግብ

የፖሊሲው ዋና ግብ የቁም እንስሳት ንግድ ለሀገራዊ የኢኮኖሚ እድገት ያለውን ጉልህ ድርሻ ማሳደግ ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር ግቦች ይኖሩታል።

- ያደገ የቁም እንስሳት የወጪ ንግድ ምንዛሪ ገቢ
- ተወዳዳሪ የሀገር ውስጥ እና የወጪ ቁም እንስሳት ንግድ
- የቀነሰ የቁም እንስሳት ህገ ወጥና ኮንትሮባንድ ንግድ
- የላቀ የቁም እንስሳት ዘርፍ የንግድ ተዋናዮች ተጠቃሚነት
- የቁም እንስሳት ግብይትን የሚያሳልጥ ጥራቱ የተጠበቀ እና ተደራሽ የገበያ መሰረት ልማትና ሎጀስቲክስ አቅርቦት

### 3.3 ዓላማዎች

የፖሊሲው ዋና ዓላማ የቁም እንስሳት ንግድ ስርዓትን በማዘመንና አቅርቦትን በማሳደግ ሀገራዊ ተወዳዳሪነትና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ነው፡፡

**ዝርዝር ዓላማዎች**

- ምቹ የቁም እንስሳት የንግድ ስርዓት መፍጠር፣
- የሀገር ውስጥ እና የወጪ የቁም እንስሳት ንግድን ማሰለጥ ፣
- የቁም እንስሳት ንግድ የማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት፣
- የቁም እንስሳትን የወጪ ንግድ መዳረሻ ገበያ ማስፋትና ትስስር ማሳደግ
- በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው የቁም እንስሳት የግብይት መሰረተ ልማት እና ሎጀስቲክስ ማሟላት፣

## 3.4 መርሆዎች

- **ተጠቃሚነት፡-** ከቁም እንስሳት ንግድ የዘርፉን ተዋናዮች ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ
- **ፍትሃዊነት እና ተወዳዳሪነት፡-** የቁም እንስሳት ንግድ ፍትሀዊና በውድድር ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ማስቻል፣
- **ጥራትና ደህንነት** ፡- ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ደረጃዎችን ያሟላ ጥራቱና ደህንነቱ የተረጋገጠ የቁም እንስሳት አቅርቦት፣
- **የዘመነ የቁም እንስሳት ንግድ ፡-** የቁም እንስሳት ንግድ በዘመናዊ ቴክኖሎጂና አሰራር የተደገፈ እንዲሆን ማስቻል፣
- **ትብብርና ቅንጅት፡-** አካባቢያዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶች፣ የትብብር ማዕቀፎችንና አሠራሮች ላይ የተመሰረተ ግንኙነትና ትብብርን መከተል፣
- **አካባቢያዊ ደህንነት፡-** ከአካባቢያዊና ተፈጥሯዊ ስነ-ምህዳር ጋር ተቃርኖ የሌለው እና የሀገሪቱን የእንስሳት ዘረ-መል ሀብትን በማይጎዳ መልኩ የተዘረጋ የቁም እንስሳት ንግድ ስርዓት፣

# 4. የፖሊሲ ጉዳዮች

የቁም እንስሳት ንግድ ሁለንተናዊ ውጤታማነቱን ለማሳደግ በፖሊሲ የተደገፈ በማድረግ እና የነበሩ አሰራር የህግ ማዕቀፎችን በማሻሻል እንዲሁም የዘርፉን የውጤት መሰኮች ባመላከተ ሁኔታ ለመፈጸም አምስት ዋና ዋና ጉዳዮች መነሻ ተደርገዋል፡፡ ይህም የቁም እንስሳት ዘላቂ ልማት እና ንግድን ለማረጋገጥ ወሳኝ ሚና የሚጫወቱ የፖሊሲ ጉዳዮች ሆነው ቀርበዋል፡፡

## 4.1 የቁም እንስሳት ግብይት ስርዓት

በሀገር ውስጥ እና በአለም አቀፍ ገበያ በዘላቂነት እና በቀጣይነት ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ የሚቻለው የግብይት ስርዓቱ ግልፅ፤ ፍትሃዊ፤ በውድድር ላይ የተመሰረተ እና የግብይት ሰንሰለቱ አጭር፣ የግብይት ወጪን ያማያንር፣ ከህገ ወጥ እና ከኮንትሮባንድ ንግድ የፀዳ፣ አትራፊ እና አዋጪ የንግድ ስነምህዳር ያለውና በዘመናዊ የግብይት ስርዓት ተደራሽ ሲሆን ነው፡፡ ሆኖም የቁም እንስሳት ግብይት ስርዓቱ ግልፅ፣ፍትሀዊ እና ተወዳዳሪ አለመሆኑ እንዲሁም የደላላ ጣልቃገብነትና የተንዛዛ የግብይት ሰንሰለት የሚስተዋልበትና የግብይት ወጪን በማናር አርብቶ አደሩ እና የንግዱ ተዋናዎች ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ያደረገ ነው፡፡

በድንበር አከባቢ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የመቆጣጠሪያ ስርዓት ባለመዘርጋቱ የቁም እንሰሳት ሀብታችን በህገ-ወጥና ኮንትሮባንድ መንገድ እንዲባከን ምቹ ሁኔታ የፈጠረ መሆኑና ለህገ-ወጥ የወጪ ምንዛሪ ዝውውር መስፋፋት መንስኤ በመሆኑ የተነሳ ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን የውጪ ምንዛሪ ገቢ አሳጥቷል፡፡ ስለዚህ ዘርፉ ለኢኮኖሚው የሚያበረክተውን ድርሻ ለማሳደግ የቁም እንሰሳት ንግድ የሚጠበቀውን ሚና እንዲወጣ ምቹ የግብይት ስርዓት መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

የዘርፉን ንግድና የግብይት ስርዓቱን በማዘመንና በማሳለጥ በሀገር ውስጥም ሆነ በወጪ ገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመገኘት በድንበር አካባቢ የሚስተዋለውን ህገ-ወጥ እና ኮንትሮባንድ ንግድ ማስቆም የሚያስችል በውድድር ላይ የተመሰረተ፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈ፣ግልጽና ፍትሃዊ የቁም እንሰሳት የግብይት ስርዓት ይዘረጋል፡፡

## 4.2 የገበያ ትስስርን በማጠናከር አቅርቦትን ማሳደግ

በገበያ ውስጥ በዘላቂነት እና በቀጣይነት ተወዳዳሪ ሆኖ ለመገኘት  ጥራትን መሰረት ያደረገ ምርት እና በተመሳሳይ ሁኔታ ምርቱን ለማቅረብ ደግሞ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የተመቻቸና ሳቢ የሆነ ገበያ መኖር አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም የገበያውን ፍላጎት እና የምርቱን አቅርቦት የተጣጣመ እንዲሆን ለማስቻል ደግሞ የገበያ ትስሰር ስርዓት መዘርጋት፣ገበያዎችን ማስፋፋት እና ምርትን በማስተዋወቅ አቅርቦትን ማሳለጥ አስፈላጊ ነው፡፡

የሀገር ውስጥ እና የወጪ የቁም እንሰሳት ንግድ የገበያ ትስስር ስርዓትን በማጠናከር በገበያው ፍላጎት መሰረት በመጠንና በጥራት ቀጣይነት ያለው አቅርቦትን በማሳለጥ፣ነባር መዳረሻ ገበያዎችን ጠብቆ በማቆየት እና አዳዲስ መዳረሻ ገበያዎችን በማስፋፋት በተጨማሪም የገበያ ትስስርን በማጠናከር ከዘርፉ የሚገኘውን የወጪ ምንዛሪ ገቢ ለማሳደግ የቁም እንሰሳት የወጪ ንግድ ማስፋፊያ እና የገበያ ትስሰር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

ለውጭ ገበያ የሚቀርበው የቁም እንሰሳት ምርት ገበያው በሚፈልገው ጥራትና መጠን ሆኖ እንደየመዳረሻ ገበያዎች ፍላጎትና መስፈርት የቁም እንስሳት ዱካን የተከተለ የእንስሳት ልየታና የምዝገባ ስርአት ያለው የአቅርቦት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

## 4.3 የማበረታቻ ስርዓት

በቁም እንሰሳት ንግድ የታቀዱ ውጤቶች በሚፈለገው ደረጃ ለማሳካት ካሉት ጉድለቶች መካከል ዘርፉን ለማሳደግ የማበረታቻ ስርዓት አለመኖር አንዱ ነው። ለአርብቶ አደሩም ይሁን በዘርፉ ለተሰማሩ አካላት ለቁም እንሰሳት ኢንቨስትመንትና ንግድ መስፋፋት የብድር አገልግሎት  ከተመጣጣኝ ወለድ ጋር አለመኖር፣ ለቁም እንሰሳት እርባታና ድልባ ኢንቨስትመንት የሚሆን የቦታ አቅርቦት አለመመቻቸት እና ከቀረጥ ነፃ የሆኑ ድጋፎች ባለመኖሩ ምክንያት ለህገ-ወጥና ኮንትሮባንድ ንግድ ተጋላጭ በመሆኑ ዘርፉ ካለው የሀብት አቅም አንፃር ማግኘት የሚገባውን ያህል የውጪ ምንዛሪ ገቢ ማግኘት አልተቻለም፡፡

በመሆኑም ዘርፉ በአለም አቀፍ ገበያ ተወደደዳሪ ሆኖ ለሀገር ኢኮኖሚ የሚጠበቀውን እስተዋጽኦ እንዲያበረክት ንግዱን የሚያዘምኑ፡-

- ለአርብቶ አደሩና ለቁም እንሰሳት ግብይት ተዋናዮች የግብይት አደጋ ጊዜ አስተዳደር ስርዓት ይዘረጋል፣
- የቁም እንሰሳት የብድር ዋስትና የማግኘት አቅጣጫን በመከተል አርብቶ አደሩ የቁም እንስሳቱን አቅርቦት በመጠንና በጥራት እንዲያሳድግ ይደረጋል፣
- የፋይናንስ አቅርቦት ወይም አማራጭ የፋይናንስ ስርዓት ይመቻቻል፤
- አመቺ እና ተስማሚ የቁም እንሰሳት ማጓጓዣዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ በሆነ መልኩ አንዲመቻች ይደረጋል፣
- የግሉ ዘርፍ በሰፋፊ ገበያ ተኮር የቁም እንሰሳት ኢንቨስትመንት ሥራ ላይ እንዲሰማራ የሚያስችሉ ምቹና ሳቢ የአሰራር ስርዓት እንዲኖር ከሀገራዊ ኢንቨስትመንት ፖሊሲ እና የህግ ማዕቀፎች ጋር በሚጣጣም መልኩ ተግባራዊ ይደረጋል፡ ፡
- ለቁም እንስሳት ኢንቨስትመንት የሚያስፈልግ የመሬት አቅርቦት እንዲመቻች ይደረጋል፣

## 4.4 የመሰረት ልማት እና ሎጀስቲክስ አቅርቦት

በቁም እንስሳት ግብይት ውስጥ በዘላቂነት እና በቀጣይነት ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቆየት የግብይት ስርዓቱ ምቹ፤ቀልጣፋ እና አዋጭ መሆን ይኖርበታል፡፡ የቁም እንስሳት ንግድን ለማሳለጥና ከዘርፉም የሚገኘውን ተጠቃሚነት ለማሳደግ ደረጃውን የጠበቀና ተስማሚ መሰረተ ልማትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ፣ ደረጃውን የጠበቀ የቁም እንሰሳት ማጓጓዣ ትራንስፖርት አገልግሎት፣ተደራሽ የሆኑ ግብይት ማዕከላት ፣የቁም እንስሳት ማቆያ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው የኳራንቲን ጣቢያዎች በበቂ መጠን አለመኖራቸው እና የቁም እንስሳት ንግድ በደላላ እና ህገወጦች የተተበተበ መሆኑ በዘርፉ የተጠኑ የጥናት ግኝቶች ያመላክታሉ፡፡
የቁም እንስሳትን በጥራት ለማቅረብና የንግድ ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ ተደራሽ የሆኑ ግብይት ማዕከላት በበቂ መገንባትና የቁም እንሰሳት ማቆያ በጉምሩክ ኬላዎች በበቂ ሁኔታ መሟላታቸው አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ ለመሆን ጥራትና ደረጃቸውን የጠበቁ የቁም እንስሳት ለማቅረብ እንዲቻል በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው የኳራንቲን ጣቢያዎች ሊሟሉ ይገባል፡፡በሌላ በኩል ጤንነቱ የተጠበቀ እና የቁም እንስሳትን ከብክለት ለመከላከል የሚያስችል ለቁም እንሰሳት ተስማሚ እና ምቹ የሆነ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ አቅርቦት መሟላት ይኖርባቸዋል ፡፡

የቁም እንስሳት የግብይት ስርዓቱን ግልፅ፣ ፍትሃዊና በውድድር ላይ የተመሠረተ በማድረግ የግብይት ሰንሰለቱን በማሳጠር ለደላላና ለህገ-ወጦች ያልተጋለጠ፣ በአምራቹ እና በተጠቃሚው መካከል ለሚደረገው ግብይት ምቹና ተደራሽ የሆኑ የግብይት ማዕከላት መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡

የገዢ ሀገራትን ፍላጎትና መስፈርት የሚያሟላና ጤንነቱ የተጠበቀ እና ጥራቱ የተረጋገጠ የቁም እንሳሳትን ለማቅረብ ደረጃውን የጠበቀ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው የቁም እንስሳት ኳራንቲን አገልግሎት የሚሰጡ ጣቢያዎች

እና በደረቅ ወደቦችና በጉምሩክ ኬላ አካባቢዎች ለቁም እንስሳት ድህንነትና ጤንነት አገልግሎት አሰጣጥ ምቹ የሆኑ ደረጃቸውን የጠበቁ የቁም እንስሳት ማቆያ ማዕከላት እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡

## 4.5 ተቋማዊ ቅንጅትና ትብብር

የቁም እንስሳት ንግድ የተለያዩ ተቋማትን ቅንጀት እና ትብብርን የሚፈልግ ነው፡፡ የዘርፉን የንግድ አሠራር ለማሳለጥ የተቋማትን ስልጣንና ተግባር በማይቃረን እና የጋራ ሃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ መፈጸም የቁም እንስሳት ንግድ ለኢኮኖሚው የሚያበረክተውን ድርሻ ለማሳደግ የጋራ ርብርብ የሚጠይቅ ወሳኝ ተልዕኮ ነው።

የቁም እንስሳት ንግድ ስርዓትን በትብብርና በቅንጀት መፈፀም በቁም እንስሳት ንግድ ስርዓቱ ላይ የጋራ መግባባት ለመያዝ እና ከወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር በማስተሳሰር እና በማጠናከር መልካም አጋጣሚዎችን በመጠቀም ውጤት ለማስመዝገብ ያግዛል፡፡

የተጠናከረ የኬላዎችና የጉምሩክ ማስተላለፊያ ጣቢያዎች ቁጥጥር ስርዓት በመዘርጋት ለቁም እንስሳት ንግዱ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸውን የፌደራል፣የክልሎች እና የግሉ ዘርፍ አካላት ጋር በቅንጅትና በትብብር ይሠራል፡፡ ተጨማሪም የአካባቢያዊ፣አህጉራዊ እና አለም አለም አቀፋዊ እንዲሁም ከልማት አጋሮች ጋር የትብብርና የቅንጅት አሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

## 5. የፖሊሲው የውጤት መስክ

- በጥራትና በመጠን ያደገ የሀገር ውስጥ እና የወጪ ንግድ የቁም እንስሳት አቅርቦት
- ውጤታማ እና ተወዳዳሪ የሆነ የቁም እንስሳት የገበያ መሰረተ ልማት
- ያደገ የቁም እንሳሳት ንግድ እና ኢንቨስትመንት

## 6. የፖሊሲው ወሰን

የቁም እንስሳት ፖሊሲ በግመል፤በፍየል፣በግ እና ቀንድ ከብት የሀገር ውስጥና እና የወጪ ንግድ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡

## 7. ፖሊሲ የማውጣት ስልጣን

ይህን የቁም እንሰሳት ንግድ ፖሊሲ የማጽደቅ ስልጣን ያለው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ነው፡፡

## 8. የፖሊሲው የትግበራ ማዕቀፍ

### 8.1 ፈጻሚ ተቋማት

የቁም እንስሳት ንግድ ፖሊሲን ተግባራዊ ለማድረግ የሚከተሉት ተቋማት በፈፃሚነት ተመላክተዋል፡፡

- **ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር፡-** የቁም እንስሳት ንግድ ፖሊሲ ያዘጋጃል፣ የግብይት ሥርዓት ይዘረጋል፣ የግብይት ማዕከላትን ያጠናክራል ያስፋፋል፣ በአህጉራዊና በዓለም አቀፍ ገበያዎች የኢትዮጵያን የቁም እንስሳት ምርት ያስተዋውቃል፣ የገበያ መዳረሻዎችን ያፈላልጋል፣ አዳዲስ ገበያዎችን ያስፋፋል፣ እንዲሁም ከሌሎች ተቋማትና ከክልሎች ጋር ትብብርና ቅንጅታዊ አሠራርን ያጠናክራል፣

- **ግብርና ሚኒስቴር፡-** የቁም እንስሳትን ልማት በማስፋፋትና ምርትና ምርታማነትን ያሻሽላል ያሳድጋል ፣የቁም እንስሳት ደህንነት እና ጤና የተረጋገጠ እንዲሆን ለማስቻል የኳራንታይን አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎችን የተሟሉ ያደርጋል እና የአቅም ግንባታ ስራዎችን ያከናውናል.፣
- **ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር፡-** ለቁም እንስሳት ንግድ አመቺ የሆነ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ ተሽከርካሪዎች እንዲሟሉ ስርዓት ይዘረጋል፤ እንዲሁም አዋጭና ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው የትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ አቅርቦትን የሚያሟላ አሰራር እንዲጠናከር ያደርጋል፣
- **የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፡-** የቁም እንስሳት ዘርፍ ለሀገራዊ ኢኮኖሚ የሚያበረክተውን ድርሻ ለማሳደግ እንዲቻል በቁም እንስሳት ኢንቨስትመንት የሚሰማሩ አልሚዎችን ያበረታታል፣
- **የጉምሩክ ኮሚሽን**፡- የቁም እንስሳት ኮንትሮባንድ ንግድ ይቆጣጠራል፣የአሠራር ስርዓት ይዘረጋል
- **የፋይናንስ ተቋማት፡-** ለቁም እንስሳት ንግድና ኢንቨስትመንት መስፋፋት የፋይናንስ አቅርቦት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራሉ እንዲሁም ከታክስ ነፃ ማበረታቻ ስርዓት ያመቻቻሉ፤ የቁም እንስሳት የመድን ዋስትና ይሰጣሉ፣ እንዲሁም የገበያ አደጋ ጊዜ አስተዳደር አሠራር ስርዓት ይዘረጋል፡
- **የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፡-**የቁም እንስሳት የወጪ ንግድ ዙሪያ ለገዢ ሀገራት ግንዛቤ ይፈጥራል፣ ምርትን ያስተዋውቃል፤

### 8.2. የህግ ማዕቀፍ

በቁም እንስሳት ንግድ የሚታየውን የግብይትና የገበያ መሰረተ ልማት፣የማበረታቻ ስርዓት እና የቅንጅታዊ አሠራር፣ የህገወጥና ኮንትሮባንድ ንግድ መስፋፋት ችግር ለመፍታት በሥራ ላይ ያሉ የሕግ ማዕቀፎች ማለትም የቁም እንስሳት ግብይት አዋጅ እና የቁም እንስሳት ግብይት ደንብ እንዲሻሻሉ ይደረጋል፡፡

የቁም እንሳሳት ንግድ ዘርፉ በተጠናከረ ተቋማዊ አደረጃጀት እንዲመራ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ደረጃ ፖሊሲውን ማስፈፀም በሚያስችል ሁኔታ እንዲደራጅ ይደረጋል፡፡ በክልሎችም ዘርፉን በውጤታማነት መምራት የሚያስችል ተቋማዊ አደረጃጀት እንዲኖር በቅንጅት ይሠራል፡፡

የቁም እንስሳት ንግድ የተወሳሰበና ዘርፈ ብዙ ችግሮች የሚስተዋሉበት በመሆኑ እና እነዚህን ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታት የሚያጋጥም የፋይናንስ አቅርቦት ችግርን ለመፍታት የልማት አጋር አካላት ትብብርን የማጠናከር ሥራ ይሠራል፣

በአካባቢያዊ፣ቀጣናዊ እና አለም አቀፋዊ የንግድ ስምምነቶችና የህግ ማዕቀፎች መሰረት የሁለትዮሽ ስምምነት እና የአፍሪካ አህጉራዊ የነጻ ንግድ ቀጣና ስምምነት፤ ቀጣናዊ የንግድ ትስስርን የሚያስርጹ ቅንጅታዊ አሰራሮች እንዲጠናከሩ የሚቀርቡ የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፎችን በማስተባበር የጋራ ተጠቃሚነትን በሚያረጋግጥ መልኩ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

### 8.3. የልማት ፕሮግራሞች

በፖሊሲው የተመላከቱ ውጤቶችን በማሳካት ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ኢኮኖሚዊ ድርሻ ለማሳደግና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ይህ ፖሊሲ በ4 ዋና ዋና ፕሮግራሞች እና በ9 ንኡሳን ፕሮግራሞች የተቀረፀ ሲሆን እነዚህን ፕሮግራሞች በዕቅድ አስደግፎ በመፈጸም በዘርፉ የሚታዩትን ተግዳሮቶች በዘላቂነት ለመፍታት በየደረጃው ያለውን ባለድርሻ አካላት በማቀናጀት እና በማስተባበር ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**ፕሮግራም1.** የቁም እንስሳት ዘመናዊ የግብይት ስርዓት ልማት፤

ይህ ፕሮግራም ሦስት ንዑሳን ፕሮግራሞች ይኖሩታል ፡፡ እነርሱም የቁም እንስሳት የግብይት መረጃ ስርዓት ማልማት፣ ሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት የግብይት ማዕከላትን ማጠናከር እና ማልማት እና የቁም እንስሳት የገበያ ትስስር ስርዓት መዘርጋት ናቸው፡፡

**ፕሮግራም 2.** ግልፅ፤ፍትሃዊ እና በውድድር ላይ የተመሰረተ የቁም እንስሳት የንግድ ስርዓት ፤

ይህ ፕሮግራም ሦስት ንዑሳን ፕሮግራሞች ይኖሩታል፡፡ እነርሱም በቁም እንስሳት ንግድ እና ኢንቨስትመንት ለተሰማራውን የግሉ ዘርፍ አቅም ማሳደግ፤ በወደቦችና፤ በጉምሩክ ኬላዎች የቁም እንስሳት ማቆያ ግንባታ እና የቁም እንስሳት የግብይት አደጋ አስተዳደር ስርዓት ዝርጋታ ናቸው፡፡

**ፕሮግራም 3**. ምቹ እና ተደራሽ የቁም እንስሳት የገበያ መሰረተ ልማት ዝርጋታ፤

ይህ ፕሮግራም ሁለት ንዑሳን ፕሮግራሞች ይኖሩታል ፡፡ እነርሱም ምቹ እና ተስማሚ የቁም እንስሳት የማጓጓዣ አግልግሎት አቅርቦት እና ደረጃውን የጠበቀና የተሟላ የቁም እንስሳት ኳራንታይን አገልግሎት ጣቢዎችን ማልማት ናቸው፡፡

**ፕሮግራም 4**.የቁም እንሳሳት ንግድ እና የእንቨስትመንት ልማት ፤

ይህ ፕሮግራም የቁም እንስሳት እርባታ እና የቄራ ኢንቨስትመንት ልማትን የያዘ ነው ፡፡

## 8.4. ክትትልና ግምገማ

ከሚመለከታችው ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅትና ትብብር በማጠናከር በፖሊሲው የተቀመጡ የፖሊሲ አቅጣጫዎች፤ ውጤቶች፤ፕሮግራሞች እና የህግ ማዕቀፎች ላይ የአፈፃፀም ክትትል ይደረጋል፣

ከፖሊሲው የሚመነጩ አስተራቴጂክ እና አመታዊ ዕቅዶች ይዘጋጃሉ፤ ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመገመገም የጋራ መግባባት ተፈጥሮበት ወደ ተግባር እንዲሸጋገር ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም አፈፃፀሙ በጋራ መድረኮች ይገመገማል፤ በአፈፃፀም ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመለየት የመፍትሄ እርምጃ ይወሰዳል፡፡

በፖሊሲው የተቀመጡ ውጤቶች በጥራትና በመጠን ያደገ የሀገር ውስጥ እና የወጪ ንግድ የቁም እንሰሳት አቅርቦት፤ ውጤታማ እና ተወዳዳሪ የሆነ የቁም እንሰሳት የገበያ መሰረት ልማት እና ያደገ የቁም እንሳሳት ንግድ እና ኢንቨስትመንት የአፈፃጸም መለኪያዎች ተዘጋጅቶላቸው በየወቅቱ እየተገመገሙ እና እየተለኩ የመጣውን ለውጥ ወይም ተግዳሮት በመለየት የመፍትሄ አቅጣጫ ይቀመጥላቸዋል፡፡

አካባቢዊ፤ አህጉራዊ እና አለም አቀፋዊ የቁም እንሰሳት መዳረሻ ገበያዎች የንግድ እንቅስቃሴ እና ሂደትን በየወቅቱ የተጠናከረ ግንኙነት በማድረግ በንግዱ ዙሪያ ያለውን ድክመት፤ ጥንካሬ፤ ያጋጠሙ ተግዳሮቶች እና ተጨማሪ የገዢ ሀገራት መስፈርቶችንና ህጎች ጋር የተጣጣመ መሆኑን ጭምር ግብረ መልስ በመቀበል እና በመገምገም የመፍትሄ እርምጃ ይወሰዳል፡፡

ለፖሊሲው መነሻ ሆኑ ተግዳሮቶች በምን ያህል ደረጃ እንደቀነሱ በክልል አካባቢዎች፤ በድንበር አካባቢዎች፤በግብይት ማዕከላት እና በገበያ መሰረት ልማት ባሉባቸው አካባቢዎች የዳሰሳ ጥናት በማድረግ በጥናቱ ግኝት መሰረት የማስተካከያ እርምጃዎች የሚወሰዱ ይሆናል፡፡ በዚህም አሰፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፖሊሲው እንዲሻሻል ይደረጋል።

## 9. ሌሎች ተያያዥ ፖሊሲዎች

የዚህ ፖሊሲ ተፈፃሚነት ከዚህ በታች ከተገለፁት ፖሊሲዎች ጋር በቅንጅት ይሆናል

- የንግድ
- የአምራች ኢንዱስትሪዎች ልማት
- የጤና
- የምግብና መድኃኒት ደህንነት
- የከተሞችና መሰረተ ልማት ዝርጋታ
- የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ
- የግብርናና ገጠር ልማት

## 10. የፖሊሲው ስርጭት

የፀደቀው የፖሊሲ ሰነድ በህትመት፣በሶፍት ኮፒ እና ሌሎች መገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ለባለድርሻ አካላት እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

## 11. ፖሊሲው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ፖሊሲው በሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ ከፀደቀበት ከ-------ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 12. የቃላት ፍች

- የእንስሳት፡- እንደ ላሞች፣ በግ፣ፍየል እና ግመል የመሳሰሉት እንስሳት በገቢ ምንጭነት የሚያገለግሉ ወይም ለውጭ ገበያ የሚሸጡ።
- አህጉራዊ ውህደት፡- ሰላም፣ መረጋጋትና ሀብትን ለማስፈን ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሃገራት ተባብረው ተቀራርበው ለመሥራት የተስማሙበት ሂደት ነው።
- ዱካን የተከተለ፡- በምርት ልማት ውስጥ የምርት ዑደት  ያለውን ማንኛውንም ነገር የመከታተል እና መስፈርቶችን የመከታተል የሚያስችል ማለት ነው።
- ንግድ፡ በጅምላም ሆነ በችርቻሮ፣ በአገር ውስጥ ወይም በውጭ ሸቀጦችን የመግዛት፣ የመሸጥ ወይም የመለዋወጥ ተግባር ወይም ሂደት ነው፡፡
- የንግድ ነፃነት፡- በአገሮች መካከል የሚደረጉ የነፃ የሸቀጥ ልውውጥ ገደቦችን ማስወገድ ወይም መቀነስ ነው።